**ያለማዳላት እና ዕኩል ዕድል ፖሊሲ**

የVEC የሰው ሀብት አስተዳደር አገልግሎቶች
ማጣቀሻ: ከታች ይመልከቱ
የተፈጻሚነት ቀን: ሐምሌ 1, 2018 ዓ.ም
ሕግ: ያለማዳላት እና የዕኩል ዕድል ፖሊሲ
ግንቦት 1, 2010 ዓ.ም

**ፖሊሲ**

ለሁሉም ሰራተኞች እና የስራ ቅጥር አመልካቾች ያለ ምንም ዘርን፣ ቀለምን፣ ሀይማኖትን፣ ጾታን፣ ጾታዊ መገለጫን፣ የጾታ ማንነት ወይም መገለጫን፣ ብሔራዊ ማንነትን፣ ዕድሜን፣ አካል ጉዳተኝነትን፣ የዘር ሀረግን ወይም የፖለቲካ ግንኙነትን መሰረት ማድረግ ዕኩል የስራ ቅጥር ዕድሎች ማቅረብ የቨርጂንያ የሥራ ቅጥር ኮሚሽን (VEC) ፖሊሲ ነው። ፖሊሲው ለዘመቻ ተመላሾች ተገቢ የስራ ቅጥር ምርጫዎችን የሚፈቅድ ከመሆኑም በተጨማሪ በተለይም ከዘመቻ ተመላሾች ላይ የሚፈጸም መድልዎን ይከለክላል።

ይህ ፖሊሲ ቅጥርን፣ ክፍያን፣ ጥቅማ ጥቅሞችን፣ የስራ ምደባዎችን፣ ግምገማዎችን፣ የደረጃ እድገትን፣ ዝውውርን፣ የሥነ ምግባር እርምጃዎችን፣ የትምህርት ድጋፍን፣ ስልጠናን፣ የማህበራዊና መዝናኛ ፕሮግራሞችን እና የVECን አገልግሎት መስጫዎችን መጠቀምን ጨምሮ በሁሉም የቅጥር ድንጋጌዎች፣ ሁኔታዎችና ቅደም ተከተሎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። ፖሊሲው ለየትኛውም አመልካች አማራጭ ለመፍጠር በቀናነት የሚጠየቁ የስራ መስፈርቶችና የብቃት ደረጃ/ችሎታ ደረጃዎችን ዝቅ ማድረግን ይከለክላል።

ከስራ ቅጥር የዕኩል ዕድል ቁርጠኝነት በተጨማሪ VEC በ1964 የሲቪል መብቶች ሕግ ርዕሥ VI፣ በአሜሪካውያን አካል ጉዳተኞች ሕግ ርዕስ II፣ 29 CFR ክፍል 37 እና ሌሎች ተገቢ መመሪያዎች መሰረት ዕኩል ዕድል መስጠት አለበት። ለዚህም አላማ የትኛውም ሰው በዘሩ፣ ቀለሙ፣ ሀይማኖቱ፣ ጾታው፣ ብሄራዊ ማንነቱ፣ እደሜው፣ አካል ጉዳተኝነቱ፣ የፖለቲካ ግንኙነቱ ወይም አመለካከቱ፣ እና ለተጠቃሚዎች ብቻ በዜግነቱ ወይም ተሳትፎው ምክንያት ከተሳትፎ መገለል፣ ጥቅማ ጥቅሞችን መከልከል የለበትም፣ ወይም በየትኛውም የVEC ፕሮግራም ወይም ተግባር ላይ ለመድልዎ መጋለጥ የለበትም።

**መነሻ**

(1) የ1964 የሲቪል መብቶች ሕግ ርዕስ VI እና ርዕስ VII፣
(2) የ1991 የሲቪል መብቶች ሕግ
(3) የገዥው አስተዳደራዊ ትእዛዝ ቁጥር አንድ (2018)
(4) 29 CFR ክፍል 38
(5) የማቋቋሚያ ሕግ ክፍል 504
(6) የአሜሪካውያን አካል ጉዳተኞች ሕግ ርዕስ I እና ርዕስ II፣ እና የአሜሪካውያን አካል ጉዳተኞች የማሻሻያዎች ሕግ
(7) የዘር ሀረግ መረጃ ያለማዳላት ሕግ ርዕስ II

በሰራተኛ ሀይል የፈጠራና ዕድል ሕግ (WIOA) ስር በዩናይትድ ስቴትስ የሰራተኛ-አሰሪ መምሪያ የገንዘብ ድጋፍ በሚደረግላቸው ፕሮግራሞችና ተግባሮች ላይ የፌደራል የዕኩል ዕድል ሕጎችና ደንቦች ተፈጻሚ ይደረግባቸዋል። VEC የፌደራል የገንዘብ ድጋፍ ተቀባይ እንደመሆኑ የሰራተኛ ሀይል የፈጠራና ዕድል ሕግ የያለማዳላት እና የእኩል ዕድል ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ አለበት።

የWIOA ክፍል 188 በዘር፣ ቀለም፣ ሀይማኖት፣ ጾታ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ እድሜ፣ አካል ጉዳተኝነት፣ የፖለቲካ ግንኙነት ወይም አመለካከት፣ እና ለተጠቃሚዎች ብቻ በዜግነት ወይም በWIOA ፕሮግራሞች ተሳትፎ መነሻነት የሚፈጸም መድልዎን ይከለክላል።

የገዥው አስተዳደራዊ ትእዛዝ ቁጥር አንድ (2018) ዘርን፣ ጾታን፣ ቀለምን፣ ብሔራዊ ማንነትን፣ ሀይማኖትን፣ ዕድሜን ወይም የፖለቲካ አመለካከትን መነሻ አድርጎ በስራ ቅጥር ላይ የሚፈጸም፣ ወይም ብቁ በሆኑ አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸም መድልዎን ይከለክላል። ፖሊሲው ለዘመቻ ተመላሾች ተገቢ የስራ ቅጥር ምርጫዎችን የሚፈቅድ ሆኖ በተለይም በዘመቻ ተመላሾች ላይ የሚፈጸም አድልዎን ይከለክላል። ለግዛት የስራ ቅጥር ለየትኛውም የግዛት ሰራተኛ ወይም አመልካች ምርጫ ለመስጠት ሲባል በቀና መንፈስ ተመስርተው የሚዘጋጁ መስፈርቶችን፣ የአፈጻጸም ደረጃዎችን ወይም የብቁነት ደረጃዎችን ማሳነስ አይፈቀድም ወይም አያስፈልግም።

*ሥነ ሥርአቶች*

*ሀ.* ማስታወቂያ

1. ለሁሉም ሰራተኞች፣ የሥራ ቅጥር አመልካቾች እና ደንበኞች ስለዚህ ፖሊሲ መገለጽ አለበት።
   - ሀ. በሁሉም የVEC ቢሮዎች ውስጥ የኤጀንሲውን "የዕኩል ዕድል ሕግ" ፖስተሮች በመለጠፍ ለደንበኞች ስለዚህ ፖሊሲ መገለጽ አለበት።
   - ለ. ለአዲስ ሰራተኞች (መደበኛና የጉልበት ስራ) በቅጥር ወቅት የፖሊሲው ኮፒ መሰጠት አለበት።
   - ሐ. ለወቅታዊ ሰራተኞች በፖሊሲው ላይ የሚደረጉ ለውጦች መገለጽ አለባቸው።

ለ. የመድልዎ ቅሬታዎች

ሰራተኞችና የስራ ቅጥር አመልካቾች ለVEC EO ኦፊሰር (የሰው ሀብት ግንኙነት ሥራ አስኪያጅ) የመድልዎ ቅሬታዎች ሊያስመዘግቡ ይችላሉ። ሰራተኞችና የስራ ቅጥር አመልካቾች በተጨማሪም ለሰው ሀብት አስተዳደር መምሪያ የዕኩል የሥራ ቅጥር ዕድል አገልግሎቶች ቢሮ እና ለዩኤስ የዕኩል የስራ ቅጥር ዕድል ኮሚሽን ቅሬታዎችን ሊያስመዘግቡ ይችላሉ።

ደንበኞች (የVEC አገልግሎቶች ተቀባዮች) ቅሬታዎችን ለVEC EO ኦፊሰር ወይም ዳይሬክተር፣ ለዩኤስ የሰራተኛ-አሰሪ መምሪያ የሲቪል መብቶች ማዕከል ሊያስመዘግቡ ይችላሉ።

የትኛውም የመድልዎ ቅሬታን በሚያስመዘግብ ሰው ላይ በኤጀንሲው ስራ አመራር የበቀል እርምጃ አይወሰድበትም።

ሐ. ጥሰቶች

የትኛውም ይህን ፖሊሲ ጥሶ የሚገኝ የVEC ሰራተኛ ተገቢ የሥነ ምግባር ዕርምጃ ይወሰድበታል።

**የኤጀንሲ መብት**

የቨርጂንያ የስራ ቅጥር ኮሚሽን ይህን ፖሊሲ የመሻሻል ወይም የማስቀረት መብቱ የተጠበቀ ነው።